በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሴፕቴምበር 1-30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም ከኦክቶበር 1-31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ከኦክቶበር 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከሴፕቴምብር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ......... - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ......... - 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ......... - 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ......... - 4 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ......... - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ......... - 5 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ......... - 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ......... - 6 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ ......... - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን ......... - 7 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ......... - 8 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ......... - 8 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምብር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

የክረምቱ ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ወር የዝናቡ መጠንና ስርጭት ከሰሜን ምሥራቅ ሰሜን፣ ምሥራቅና መካከለኛ ኢትዮጵያ አካባቢዎች በመጠንና በስርጭት የሚቀንስበት ጊዜ ነው። ይሁንና በዚህ ወቅት ያለው በቂ እርጥበት አዘል አየር በፀሐይ ኃይል በመታገዝ ከሚፈጥራቸው የደመና ቁልሎች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ዝናብ እንዲኖር አስችሏል።

በመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠርና መስፋፋት አተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ተጠናክረው ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም ዝናቡ በስርጭትም ሆነ በመጠን በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎችን ያዳረሰ የዝናብ ሁኔታ ከመኖሩም ባሻገር በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በብዙ ቦታዎች ላይ አግኝተዋል፡፡ በሁለተኛዎቹ አስር ቀናት ዝናቡ በአብዛኛው የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ቀጥሎ የነበረ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም ዝናቡ ለረጅም ጊዜ ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ወደ ነበሩት ደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይም አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። በተጨማሪም በወሩ የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ዝናቡ ከሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ በመቀነስ የክረምቱን ዝናብ ሲያገኙ በቆዩት በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛውና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ የነበረው ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአብዛኛ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1)፡፡


በአጠቃላይ ባለፈው የሴፕቴምበር ወር የነበረው የክረምት ዝናብ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳረሰ ሲሆን፤ በተጨማሪም በወሩ ውስጥ አልፎ አልፎ በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋና በመጠንም ረገድ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸዉ ። ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 32.2፣ በባህር ዳር 62.5፣ በኮምቦልቻ 47.0፣ 45.4 እና 31.2፣ በጅማ 30.7 እና 37.5፣ በአልጌ 48.2፣ 40.0 እና 60.0፣ በአምደ ወርቅ 31.5 እና 44.0፣ በአንገር ጉትን 35.4፣ 30.4፣ 50.6 እና 39.4፣ በአርጆ 32.8፣ 42.6፣ 34.8፣



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

34.6፣ 41.2፣ 38.4 እና 34.2 በአርሲ ሮቤ 39.6፣ በአፅቢ 44.0 እና 40.2፣ በቡሬ 45.7 እና 60.3፣ በቻግኒ 60.4፣ 31.8 እና 32.8 በጨፋ 33.4 እና 30.6፣ በጭራ 36.7፣ በደብረ ታቦር 31.1 እና 41.1፣ በዳንግላ 37.5 እና 32.0፣ በደብረ ወርቅ 86.6፣ በሀዋሳ 63.0፣ በደምቢ ዶሎ 31.5፣ በፉኚዶ 35.0 እና 45.8፣ በጊዳ አያና 45.5፣ በጊምቢ 39.8፣ 32.9 እና 34.7 በሊሙ ገነት 54.2፣ 45.2፣ በማሻ 40.2፣ 30.5 እና 40.0፣ በሞጣ 48.6፣ በሻምቡ 42.6፣ በተርጫ 44.3፣ 38.7 እና 37.6 በሶዶ 32.6፣ በየትኖራ 34.5፣ በጨለንቆ 55.3፣ በቡለን 40.2 እና 33.1፣ በቢሸፍቱ 31.2፣ በነቀምቴ 36.5፣ 34.3 እና 36.0፣ በአይራ 34.0፣ በባቲ 78.0፣ በበደሌ 36.6፣ 38.4 34.2 እና 33.8፣ በፉኚዶ 49.8፣ በጋምቤላ 59.0፣ በካቺሴ 64.2፣ በማጂ 50.0፣ በመተማ 48.1 እና 40.4፣ በቴፒ 29.7፣ በላንጌ 42.5፣ በደብረ ማርቆስ 42.2፣ በአቦቦ 30.4፣ በአለምከተማ 32.2፣ በአለም ተፈሪ 52.4፣ በአማን 34.9፣ በገለምሶ 43.0፣ በጉንዶ መስቀል 30.0፣ በሽርቆሌ 36.0፣ በሂርና 46.0፣ በጨለንቆ 35.0 እንዲሁም በካራሚሌ 34.6 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፈው የሴፕቴምበር ወር በ53 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፣ በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይም በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-86.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በ32 የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡







ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፈው የሴፕቴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኙዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን እና የሀላባ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የወላይታ፣ የጋሞ፣ የጌዲኦ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ ከ81-550 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ9-30 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ከትግራይ የመካከለኛው፣ የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ዞኖች፤ ከአማራ ሰሜን ወሎ እና ዋግህምራ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ እንዲሁም ቦረናና ምስራቅ ቦረና፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ፣ አውሲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ ከሶማሌ የሲቲና ፋፈን ዞኖች፤ የኤረር፣ ነጎብ፣ ጃረር የቆራሂ፣ የሸበል፣ የዶሎ፣ የአፍዲር፣ የሊበንና እና የዳዋ ዞኖች እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ5-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ9 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፈው የሴፕቴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ፣ ምስራቅና ምዕራብ አማራ፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፤ የጋምቤላ ክልል፤ የምዕራብ፣ የመካከለኛውና የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፤ የአፋር ክልል፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ የሊበንና እና የዳዋ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት በተለያየ የእድገት ደረጃ ለሚገኙ አዝርዕቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተለይም፡-

- በማበብና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ አዝርዕቶች፣
- ቀደም ብለው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣
- ለቋሚ ተክሎች እና ለፍራፍሬዎች እንዲሁም ለጓሮ አትክልቶች የዉሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡

በሌላም በኩል በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ በሰሜን ሸዋ ዞን አሳግርት ወረዳ የመሬት መንሸራተት የተከሰተ ሲሆን፤ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በዳውሮ ዞን ተርጫ ከተማ ከነበረዉ ከፍተኛ እርጥበት ጋር ተያይዞ በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ከተለያዩ የመስክ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል (ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል (ካርታ 13)፡፡ በተለይም በአባይ፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ እንዲሁም የላይኛው ገናሌ ዳዋ እና የዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ነበራቸው፡፡ በመሆኑም የነበረው የእርጥበት ሁኔታ የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር የውሃ ሃብትን ከማጎልበቱም በተጨማሪ ወደ ፊንጫ፣ ቆቃ፣ ተከዜ፣ ግልገል ጊቤ፣ እና ቦሮ ግድቦችና የውሃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከመጨመር አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ወደ ሆኑት የገናሌ ዳዋና የታችኛው የስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት መስፋፋት  የተስተዋለ ቢሆንም በአንጻሩም በአንዳንድ የምስራቅና ሰሜን ምስራቅ በሚገኙት የአፋር ደናክል፣ የአዋሽና የላይኛው ተከዜ እንዲሁም ጥቂት የላይኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው እቀነሰ መሄዱን ያመላክታል (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ድንበር ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው የበጋ ወቅት እንደሚስተዋለው የሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ከመታየቱ አንጻር የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመር ያሳያል፡፡

በመጪዉ የኦክቶበር ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና በሂደትም ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ሀይል በመታገዝ ከሚጠናከሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በጥቂት የምዕራብና በደቡብ ምዕራብ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የኦክቶበር ወር በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዕርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸውና በሂደትም ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩትና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ቀደም ብሎ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ ይኖረዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ እርጥበቱ ቀጣይነት የሚኖረው በመሆኑ ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ለመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በአካባቢው ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ ሣር ልምላሜ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በሌላ በኩል የእርጥበት እጥረት ላለባቸው አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማቀብ እና ለማሰባሰብ ምቹ ሁኔታ ስለሚኖር ይህንኑ አጋጣሚ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዉ የኦክቶበር ወር ከአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው በመጠንም ሆነ በስርጭት እየቀነሰ እንደሚሄድ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ የታችኛውና የመካከለኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውኃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የመስኖም ሆነ የሀይል ማመንጫ ግድቦችን የውኃ መጠን ከፍ ስለሚያደርግ በመጪው የበጋ ደረቅ ወራት አስተማማኝ የሀይል አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል። በተጨማሪም የታችኛውና የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ በአንጻሩ መጠነኛ የሆን የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et